# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 50 ሚያዚያ 22 2001 ዓ.ም


ኦነግ ሸበር ፈጠረ ብለው እስር ቤት አብረውን የታሰሩ ሰወችን አውጥተው የራሳቸው ወታደሮቻቸውን መሳሪያ አጠገብ አድርገው ያንን ቪዲዮ አንስተው ሽብርተኞች ከነመሳሪያቸው ያዝን ብሎ የሚዋሽ ቀጣፊ መንግስት ነው ...እስር ቤት አስረው ያስቀመጡትን ሰው በዛው ቀን ሄዶ ወጣቶች ይዞ ቤት ሲያቃጥል ነበር ብሎ ፍርድ የሚያስፈርዱ ሰወች ናቸው ...ማን ያምናቸዋል ..... ዶር ብርሃኑ ነጋ

በራሱ ሰራዊትም ይሁን በሲቪል አስተዳደሩ ውስጥ ወይንም ደግሞ ከተለያዩ ተቃዋሚ ፓርቲወች ጋር በሚገጥመው ችግር ሰው ማሰር፤ መግደል፤ ማጥፋትና ማሳደድ ልማዱ መሆኑን ስለምናውቅ ለእንዲህ አይነቱ ነገር መልስ በመስጠት ጊዜ አናጠፋም እኛ ወያኔን መታገያ ጊዜ በጣም የሚያስፈልገን ሰወች ነን...... አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ

## ወያኔ በዘር ባደራጀው ሰራዊቱ የተከሰተውን ቀውስ በግንቦት 7 ለማላከክ መሞከሩ የተለመደ የውሸት ነውረኛ ተግባር በመሆኑ ለዚህ መልስ በመስጠት የማጠፋው ጊዜ የለኝም ሲል ግንቦት 7 መግለጫ አወጣ

ወያኔ በዘር ባደራጀው የመከላኪያ ሠራዊት ውስጥ ጭምር እየተጠናከረበት ለመጣው ቀውስ ህዝብን ለማደናገርና የሚፈልጋቸውን ግለሰቦች ከስራ ለማባረር፤ ለማሰር ፤ለማሰቃየትና ለምግደል የሚጠቅምበት የተለምደ ነውረኛ ተግባሩ በምሆኑ ግንቦት 7 ለዚህ ምላሽ በመስጠት የሚያጠፋው ጊዜ እንደሌለው መግለጫ አወጣ የመግለጫው ሙሉ ቃል እንደሚከተለው ይነበባል

ቀን፡ ሚያዝያ 17/ 2001 ዓ.ም

<u>ከግንቦት 7 ለፍትህ ለነፃነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ</u>

ጉዳዩ፡ <u>ከተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን፣ በዛሬው እለት፣ ሚያዝያ 17/2001 ግንቦት 7 ንቅናቄን በሚመለከት በወያኔ የዜና አውታሮች አገዛዙ ያሰራጨውን መግለጫ በሚመለከት ለቀረቡልን ጥያቄዎች የተሰጠ ማብራሪያ፡፡</u>

የመለስ አገዛዝ በዛሬው እለት ሚያዝያ 17/ 2001 ዓ.ም ‹ራሱን የግንቦት 7 ብሎ የሚጠራው ቡደን የሽብር ሴራ ከሸፈ› በማለት ያወጣውን መግለጫ አንብበነዋል፡፡ የመለስ አገዛዝ በተለያዩ ወቅቶች በህዝብ ውስጥ ተቃወሞ ሲበዛበት፣ የተቃዋሚ ድርጅቶች አፋጠው ሲይዙት፣ በገዛ ሰራዊቱና በሲቪል አስተዳደሩ ውስጥ ችግር በገጠመው ቁጥር ፣ህዘብን ለማደናገር ወይም የሚፈልጋቸውን ግለሰቦችና ቡድኖች ለማጥቃት ሰፈልግ እንዲህ አይነቱን መግለጫ ማውጣትና ህዝብን ማደናገር፣ መግለጫውን ተከትሎ የሚፈልገውን መግደል ፣ማሰር፣ ከስራ ማባረር ፣ከቀየው ማፈናቀልና ማሳደድ ባለፉት አስራ ስምንት አመታት እድሜው ደጋግሞ ሲፈጽመው የኖረ ነውረኛ ድርጊቱ እንደሆነ ይታወቃል፡፡

ይህ በዛሬው እለት ግንቦት 7 ንቅናቄን በሚመለከት ያወጣው መግለጫ ከእዚህ በፊቱ ወያኔ ሲያወጣው ከነበሩት መግለጫዎች ልዩነት የሌለው መሆኑን ንቅናቄያችን ይገልፃል፡፡ የሚይዘው የሚጨብጠው ያጣው የመለስ አገዛዝ የግንቦት 7ን ንቅናቄ በማንሳት አንዴ በሰላም እንንቀሳቀሳለን የሚሉ ድርጀት አባላት በስውር የግንቦት ሰባት አባላት ናቸው የሚል የስም ዝርዝር ሲያወጣ፣ አንዴም እነዚህ ከበርቴዎች ግንቦት ሰባትን ይደግፋሉ በማለት የማሸበሪያ ወረቀት ውስጥ ውስጡን ሲበትንና ባለሃብቶቹን ሲዘርፍ፣ አሁን ደግሞ የተወሰኑ የሰራዊት አበላት የግንቦት ሰባት ሰዎች ሆነው ተገኙ ብሎ በሬድዮና በቴለቪዝን ሲያስተገባ ግንቦት ሰባት ንቅናቄ እየተነሳ ምላሽ በመስጠት የሚያጠፋው ጊዜ እንደሌለው ለማሳወቅ እንወዳለን፡፡

ንቅናቄያችን እንደተገነዘበው ግንቦት 7 ለመለስ ዜናዊና በአምባገነናዊ ክበቡ ለተሰባሰቡት ጥቂት ዘረኞች እንቅልፍ የነሳቸው ድርጅት መሆኑን ብቻ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ተገቢ ነው፡፡ንቅናቄያችን የወያኔን ማስፈራሪያ ክስና ሌላም ነገር ፈርቶ ይህን ዘረኛ አምባገነን ሰርአት ከሃገራችን ህዝብ ጫንቃ ላይ በማንሳት ህዝብ የሃገሩና የህይወቱ ባለቤት የሚሆንበትን መራራ ትግል በማድረግ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለመፍጠር የጀመረውን ፍልሚያ አጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን ወዳጅም ሆነ በመለስ ዜናዊ ስር የተሰባሰቡት አማባገነን ዘረኞችና ደጋፊዎቻቸው ሊያውቁት ይገባል፡፡

ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ
ሚያዚያ 17/2001 ዓ.ም

## ግዜ — ግንቦት 7 ዜና

**ወያኔ በመፈንቅለ መንግሥት ሴራ ከተከሰሱት ብርጋዴር ጀነራል ተፈራ ማሞ ጋር ንኪኪ ይኖራቸዋል በሚል ጥርጣሬ በአገር መከላከያ ሠራዊት ውስጥ ክከፍተኛ እስከ ዝቅተኛ ማዕረግ ያላቸውን የመመንጠር ዘመቻ ተያይዞአል ። በጥቃቱ አማርኛ ተናጋሪው ዋና ስለባ እንደሆነ ከወያኔ ደህንነት መ/ቤት አካባቢና ወታደራዊ ምንጭ የተገኘ የ'እንትለጀንስ መረጃ አጋለጠ ።**

መፈንቅለ መንግስት ሊሞከርብኝ ነበር ያለው ዘረኛው የመለስ አገዛዝ ብዛት ያላቸውን የመከላከያ ሰራዊት ሀላፊዎች እና አባላት በስፋት ማሰር መቀጠሉን የግንቦት ሰባት ወታደራዊ ምንጮች ገለጹ።እንደወታደራዊ ምንጮቻችን ገለጻ የጅምላ እስሩ በዋነኛነት የአማራ ተወላጅ የሆኑ የከፍተኛ፤ መካከለኛ እና ዝቅተኛ መኮንኖችን ኢላማ እንዳደረገ አስረድተዋል።

ለጠቅላይ ሚንስትር ጽ/ቤት ቅርበት ያላቸው ምንጮቻችን እንደገለጹት፤ የአማራ ብሄር ተወላጅ የሆኑትና በአማራው ጦር ውስጥ ታላቅ ተሰሚነት ያላቸው ብርጋዴር ጄኔራል ተፈራ ማሞ "ከግንቦት 7 ንቅናቄ ጋር ተመሳጥረው መፈንቅለ መንግሥት ሊያደርጉብኝ ነው" በማለት ወያኔ ከከሰሳቸው ካለፈው አርብ ወዲህ የወያኔ ደህንነት ሃላፊዎችና ለመለስ ቅርበት ያላቸው የህወአት ሹመኞች በወያኔ ጠቅላይ ሚንስቴር ጽ/ቤት ተሰባስበው አማርኛ ተናጋሪ የሆነው ሁሉ የሴራው ተባባሪ ሊሆን ይችላል በሚል ስጋት በሥራ ላይ የሚገኘውን ጦር ሙሉ በሙሉ በአዲስ ምልምል ወታደሮች ለመተካት የሚቻልበት ስልት ላይ ከተወያዩ ቦኋላ እንዲህ አይነቱ እርምጃ በአንድ ጊዜ መውሰዱ ተቃዋምዎች ህብረተሰቡን የሚቀሰቅሱበት ምክንያት መስጠት ስለሚሆን ለጊዜው ከ50 አለቅነት በላይ ማዕረግ ያላቸው እንዲባረሩና የተቀሩት ቀስ በቀስ በቦታቸው እስኪተኩ በራሳቸው ላይ ሂስና ግለሂስ በማድረግ እንዲታለፉ ተወስኖአል ። ....................

(ወደ ገፅ 4 ዞሯል)

**ወያኔ በዘር ባደራጀው የመከላኪያ ሠራዊት ውስጥ ጭምር እየተጠናከረበት ለመጣው ቀውስ የሰጠውን መግለጫ ግንቦት 7 አጣጣለው:: የኦፌዴን ሊቀመንበር አቶ ቡልቻ ደመቅሳም ከምርጫው በፊት ተቃዋሚን ለመመንጠር ሲባል ወያኔ የፈበረካት ሃሰተኛ ውንጀላ መሆኗን ማንም አይስተውም ሲሉ ለቪ ኦ ኤ በሰጡት ቃለ መጠይቅ ገለጹ::**

የዘረኛው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ባለፈው ቅዳሜ ለህዝብ ይፋ ባደረገው መግለጫ 35 የሚሆኑ የመከላኪያ ሰራዊት አባላትና ሲቪል ዜጎችን ለግንቦት 7 የሽብር አላማ ተባባሪዎች ሆነዋል በማለት እንዳሰራቸው ከገለጸበት ጊዜ ጀምሮ የወያኔ በሬ ወለደ ውሸት ፕርፖጋንዳ የሰለቸው የኢትዮጵያ ህዝብ ዜናውን ከመጠፍ አንዳልቆጠረው የአዲስ አበባ ዘጋቢያችን ያነጋገራቸው የከተማው ነዋሪዎች ገልጸዋል::

ወያኔ በምርጫ 97 ህዝብ የመረጣቸውን የህዝብ ተወካዮች ሰብስቦ እሥር ቤት ካስገባ በኋላ በጅምላ ለጨፈጨፋቸው ሰላማዊ ዜጎች ሞት ምክንያት ነኝ ብላችሁ ካልፈረማችሁ እና መንግሥትንና ህዝብን ይቅርታ ካልጠየቃችሁ እስር ቤት ትበሰብሳላችሁ ብሎ ይደነፋ እንደነበር ይታወሳል። የሃሰት ፕሮፖጋንዳውን በበላይነት ሊያካሂድበት የሚችልበትን አጋጣሚ በሽማግሌ ተብየዎች ጣልቃ ገብነት ካገኘ በኋላም ቢሆን እንኳ ችግሮችን ከመፍታት ይልቅ በትዕቢት ተወጥሮ «ከፈለጋችሁ በጉልበት ሞክሩኝ» ሲል የነበረ መሆኑን በማስታወስ፣ «ምነው ዛሬ በሚገባው ቋንቋ የሚያነጋግረው ብቅ ማለቱን ሲሰማ ገና ከጅምሩ «ሽብርተኛ ሽብርተኛ » እያለ ማላዘን አበዛ?» በማለት ህዝብ መሳለቅ መጀመሩን ዘጋቢያችን ከላከልን ዘገባ ለማወቅ ተችሎአል:: (ወደ ገፅ 2 ዞሯል)

**ለወያኔ በጀት ምደባ አድሎአዊነት እንዲመችና ቀጣዩን ምርጫ ተብዬ ወያኔ አንደማያሸንፍባቸው የገመታቸውን ክልሎች የህዝብ ተወካዮች ቁጥር ለመቀነስ ሲባል የተዛባውን የህዝብ ቆጠራ ውጤት የማጣራቱ ሥራ አስከ አሁን እንዳልተጀመረ ተገለጸ::**

ከአራት ወር በፊት ተጠናቆ የቀረበው አወዛጋቢው ብሄራዊ የህዝብ እና ቤቶች ቆጠራ ውጤት የአማራ እና የአዲስ አበባ ህዝብን በከፍተኛ ቁጥር ቀንሶ በማቅረቡ የተነሳ ፓርላማ ተብዬው ምርመራ ተደርጎበት በተጠቀሱት ክልሎች ዳግም ቆጠራ ይካሄዳል ብሎ የነበረ ቢሆንም እስካሁን ድረስ አንዳችም የምርመራ ሂደት እንዳልተጀመረ የውስጥ አዋቂ ምንጮች ገለጹ።

የግንቦት ሰባት ድምጽ የአዲስ አበባ ዘጋቢ የውስጥ አዋቂ ምንጮቹን ጠቅሶ እንደዘገበው የወያኔ አገዛዝ በዘረፈው የህዝብ ድምጽ ላቋቋመው ፓርላማ ቃል በገባው መሰረት ምንም እንቅስቃሴ አልጀመረም።

በ1999 በተደረገው በዚህ ቆጠራ የአማራው ህዝብ ከ2 ሚሊዮን በላይ በሚሆን ቁጥር መቀነሱ፣ ከአምስት ሚሊዮን በላይ የሚገመተው የአዲስ አበባ ህዝብም ከግማሽ በላይ ቀንሶ 2.5 ሚሊዮን መባሉ ተቀባይነት እንድሌለው በባለሙያዎች ጭምር ሲገለጽ መቆየቱ ይታወሳል።በተመሳሳይ ሁኔታ የጉራጌን ህዝብ ቁጥር ከግማሽ በላይ መቀነስ በተመለከተ አንዳንዶች ጥያቄ እያነሱ ነው። ምንም እንኳ ወያኔ ይህንን ጉዳይ ስልጤዎች ከጉራጌዎች ጋር አንድ ላይ ባለመቆጠራቸው አሳቦ በቀላሉ ማለፍ ቢችለውም፣ ስለጉዳዩ የሚነሱ ጥያቄዎችን ለማፈን የሚደረገው ሙከራ ተጨማሪ ጥያቄዎችን ማስነሳት ቀጥሏል። አንድ የጉራጌ ዞን ተመራጭ ........

(ወደ ገፅ 4 ዞሯል)

## የመጨረሻው መጀመሪያ

ከዚህ ቀደም ደግመን ደጋግመን እንደገለፅነው ግንቦት 7 ማንኛውንም ለነፃነት የሚደረግ እንቅስቃሴ ይደግፋል:: ታጋዮቹንም ያከብራል:: ጀግንነታቸውን ያደንቃል::

አሁን በኢትዮጵያችን ውስጥ ባለው አፈናና የኑሮ ውድነት ምክንያት በራስና በተለይም በወገን ላይ በሚደረግ ሰቆቃ ተማረው በግልም ሆነ በቡድን ተነሳስተው በዚህ ዘረኛና አጥፍቶ ጠፊ የወንበዴ ቡድን ላይ እርምጃ ሲወሰድ አይገርመንም:: ይህንን መሳይ ትግል ለሚያደርጉ ሁሉ ከፍተኛ አክብሮትና ወገናዊነት እንዲሚሰማን እንደገና ለማረጋገጥ እንወዳለን::

ግንቦት 7 እስከአሁን ይፋ በወጣ ትግል ያልጀመረው አስፈላጊ ዝግጅቶች ባለመደረጋቸው ሳይሆን በወገን ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳትና ኪሳራ በሚቻለው መጠን ለማስወገድ ይህም ካልሆን ለመቀነስ በማሰብ ነው::

ግንቦት 7 ይህንን ለማድረግ የሚያስችል የትግል ስልት ማጠናቀቁን እነመለስ ያውቁታል:: አውቀውም ነው ይይዙት ይጨብጡት ያጡት:: እነመለስ ሊደርሱበት የማይቻላቸው ሰፊና ሁሉን አቀፍ አደረጃጀት በመሆኑ ነው እየተርበተበቱና የሚይዙት የሚጨብጡት የጠፋቸው:: ከመደናገጣቸውም የተነሳ እጃቸው ያረፈባቸውን ወይም በሌላ ሁኔታ ያልተስሚሚቸውን ሰብስበው እስር ቤት ያጎሩት:: የ 80ና የ90 አመት አዛውንቶችን ማጥቃት የጀመሩት:: ከፈሪና ከባለጌ ድሮስ ከዚህ የተለየ ምን ይጠበቃል? ያም ሆኖ ግንቦት 7 ለዚህ አኩይ የወያኔ ተግባር ሰበብ መደረጉ እጅግ ያሳዝነዋል::

የግንቦት 7ትና የአጋሮቹ የተደራጀ እንቅስቃሴማ መኻሉን አካቶ ከዛላ አንበሳ እስከ ሞያሌ፤ ከጂካዎ እስከ ቀብሪደሐር በአንዴ ሲነሳበት በቀናት ውስጥ እንደሚያልቅለት የሚያውቀው ወያኔ ማጣፊያው እየጠፋበት ነው::

በተለይም ከውጭና ከውስጥ የሚደረጉ ጫናዎች በበረቱበትና እነዚህን ዘረኞች መያዣ መጨበጫ ባሳጡበት ወቅት፤ በአገርና በሕዝብ ላይ ባደረሱት ጭፍጨፋ አለምአቀፍ ወንጀለኞች በመሆናቸው መሸሻ እንደሌላቸው ያወቁ የአልሞት ባይ ተጋዳይ መፍጨርጨር ከፍተኛ ጉዳት ሊያስከትል ስለሚችል ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ የግድ ይላል::

ግንቦት 7 በአሁኑ ጊዜ የሚጨነቀው ለወያኔ መወገድ አይደለም:: ይህ ያለቀለት ጉዳይ በመሆኑ:: ግንቦት 7ትን እጅግ የሚያሳስበው ከወዲሁ በቂ ዝግጅት ካልተደረገ ወያኔ በወደቀ ማግስት ሊደርስ የሚችለውን ግርግርና ሊከሰት የሚችለው አደጋ ነው::

በዚህም ቢሆን ሊደርስ የሚችለውን ግርግር ገትቶ የተረጋጋ የስልጣን ሽግግር ሊደረግ የሚችልበትን ሥርዓት ከመንደፍ አኳያም የግንቦት 7 ንቅናቄአችሁ ከህዝብ ጋር እየተወያየ፤ ከትግል አጋሮቹ ጋር እየተመካከረ ሕዝብ እውነተኛው የሥልጣን ባለቤትነቱን የሚያረጋግጥበት፤ ከአሁን በኋላ እሱ ያልፈቀደውና ያልመረጠው ሥልጣኑን እንዳይቀማው የሚያረጋግጥ ሥርዓት ለማዋቀር የሚያስችል ዝግጅትም እየተከናወነ መሆኑን ነው::

እዚህ ላይ እጅግ አበረታች የሆነው ነገር አጋሮቻችንና ሌሎች የነፃነት ታጋዮች ሁሉ በዚህ ጉዳይ ላይ ፍፁማዊ መግባባት ላይ የደረሱ በመሆኑ ሁሉን አቀፍና አሳታፊ ተግባራ እየተከናወነ መሆኑን ነው::

**ወያኔ በዘር ባደራጀው የመከላኪያ ሠራዊት ውስጥ ጭምር እየተጠናከረበት ለመጣው ቀውስ .....** (ከገፅ 1 የዞረ)

ዘጋቢያችን የተለያየ የህብረተሰብ ክፍል ይወክላሉ በማለት ያነጋገራቸው ሰዎች፥ ወያኔ በድህረ ምርጫ 97 በአዲስ አበባና በተለያዩ የአገሪቱ ከተሞች በአጋዚ ጦር አማካኝነት ምንም መሳሪያ ባልታጠቁ ሰላማዊ ዜጎች ላይ ዘግናኝ ፋሽስታዊ ጭፍጨፋ ከፈጸመ በኋላ ህዝብ አንገቱን ደፍቶና ለጊዜው ተስፋ ቆርጦ እንደተቀመጠ በመጥቀስ፤ ወያኔ ሰሞኑን እራሱ በሚቆጣጠረው የአገሪቱ መገናኛ ብዙሃን እየደጋገመ የሚገልጸው የግንቦት 7 እንቅስቃሴ እውነት ከሆነ የጸሎታቸው መሰማት እንደሆነ ተናግረዋል። አንድ አስተያየት ሰጪም፥ « እያንዳንዳችን አልጋ ላይ ተኝተን ወያኔ በፈጠረው ረሃብ ከመሞት፣ ለነፃነታችን ተናንቀን በመሞት ቢያንስ ለልጆቻችን የምትሆን አገር ፈጥረን ብናልፍ ኩራታችን ነውና፤ ታሪክ ይሰራል አትጠራጠር » እንዳሉት አያይዞ ዘግቧል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ወያኔ ከየቤታቸው ለቃቅሞ መንግስቴን ሊገለብጡና ሽብር ሊያካሂዱ ሲዘጋጁ ደረስኩባቸው ብሎ ያሰራቸው ዜጎች ጉዳይ የግንቦት ሰባት አመራር አባላት ዶክተር ብርሀኑ ነጋ እና አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ “የተለመደው የወያኔ ቅጥፈት ነው » ሲሉ ለአሜሪካና ለጀርመን ድምጽ ሬዲዮኖች በሰጡት መግለጫ አስታወቁ።

የወያኔን የበሬ ወለደ ፈጠራ አስመልክቶ ከአሜሪካ ድምጽ ጥያቄ ቀርቦላቸው የነበረው ዶክተር ብርሀኑ ነጋ የመለስ አገዛዝ በደነገጠ እና በባነነ ጊዜ ሁሉ ለሚያኾጎደጉደው ክስ ማስተባባያ ለመስጠት ግንቦት 7 ጊዜ እንደሌለው ገልጸው፣ ይሄ ብካይ አምራች ኋላ ቀር ቡድን የፓለቲካ ባላንጣዎችን ለመምታት የሚጠቀምበትን መሰሪ አሰራር እስር ቤት በነበሩ ጊዜ ካዩት በመነሳት እንደሚከተለው ለቪኦኤ ተናግረዋል።

“ባጠቃላይ ይሄ መንግስት በጨነቀው ቁጥር ለሚያነሳቸው ውንጀላወች የምናጠፋው ጊዜ የለንም ይሄ መንግስት እኮ ውነት ተናግሮ አያውቅም እኔ አሁን በደረስኩበት ሁኔታ ውነትና ውሸት የሚለዩበትም ነገር ጠፍቷችዋል ነው የምለው እና የህዝቡና የተቃዋሚ ሃይሎችን ሃሳብ ለመከፋፈልና ለማዘናጋት በየጊዜው ወንጀል በፈጠረ ቁጥር ለሱ መልስ እንስጥ ብንል እሱን ታግለን ለመጣል ከምናውለው ጊዜ ማባከን ነው” ብለዋል

“በ1998 እኛ በታሰርን ጊዜ አንድ ውቅት ላይ ኦነግ ሽበር ፈጠረ ብለው እስር ቤት አብረውን የታሰሩ ሰወችን አውጥተው የራሳቸውን የወታደሮቻቸውን መሳሪያ አድርገው ያንን ቪዲዮ አንስተው ሽብርተኞች ሲፈጽሙ ከነመሳሪያቸው ብሎ የሚዋሽ ቀጣፊ መንግስት እኮን ነው ያየነው እኛን እኮ በሚዋሹበትና በሚቀባዥሩበት አይደልም የምልህ ፍርርድ ቤት እኮ አይን አውጥተው ፍርድቤቱን የሚዋሹ አብሮ ፍርድ ቤቱም በዛ ውሸት የሚሳተፍላቸው ሰወች ናችው ስለዚህ ምሳሪያ አሳዩ በቴለቭዥን አሳዩ ብትለኝ እኔ ምንም አይገርመኝም እነኝህ ሰዎች ምንም ነገር ከማድረግ ወደኋላ የማይመለሱ ነውር የሚባል የማያውቁ ሰውች ናችው የኢትዮጵያ ህዝብ ይሄንን አይቶ መሳሪያ ከነኝህ ሰዎች ተያዘ ብሎ የሚገምት አይመስለኝም እኛ እኮ ፊት ለፊት ምስክር ብለው ያመጡት ሰውየ አቃቢ ህግ በግድ እነኝህ እነኝህ ሰዎች ላይ መስክር ብሎ ስጥቶኛል ብሎ ያለ ነው እስር ቤት እኮ አስረው ያስቀመጡትን ሰው በዛው ቀን ሄዶ ወጣቶች ይዞ ቤት ሲያቃጥል ነበር ብሎ ፍርድ የሚያስፈርዱ ሰወች ናቸው እኮ ነዚህ ሰዎች የሚሉትን ነገር ማን ያምናቸዋል “

እንደዶክተር ብርሀኑ ሁሉ አቶ አንዳርጋቸውም ዘረኛ አምባገነኑ የመለስ አገዛዝ በደነገጠ እና በባነነ ቁጥር መልስ ለመስጠት የሚሆን ጊዜ ግንቦት ሰባት እንደሌለው አስታውሰው፣ የመለስ ቡድን ግን ያደገበትን ዜጎችን የማሰቃየት፣ የማሰር እና በበሬ ወለደ ፈጠራ መክሰስ ጭራሹኑ እንደማያስገርማቸው ለጀርመን ድምጽ እንደሚከተለው ተናግረዋል።
“እንዲህ አይነት መግለጫ በተደጋጋሚ በማውጣት በራሱ ሰራዊትም ይሁን በሲቪል አስተዳደሩ ውስጥ ወይንም ደግሞ ከተለያዩ ተቃዋሚ ፓርቲወች ጋር በሚገጥመው ችግር ሰው ማሰር መግደል ማጥፋት ማሳደድ ልማዱ መሆኑን ስለምናውቅ ለዲህ አይነቱ ነገር መልስ አንሰጥም ምክንያቱም ወያኔ ጊዜ ሞልቶታል እኛ ደግሞ ወያኔን መታገያ ጊዜ በጣም የሚያስፈልገን ሰወች ስለሆንን በየጊዜው ለሚቀርብ ትርጉም ያለው ጉዳይ ስላልሆነ መልስ አንስጥም ብለናል በዚሁ ነው የምንቀጥለውም” ብለዋል
ወያኔ ከሰማንያ አመት አዛውንት አንስቶ እስከ አፍላ ወጣቶች ድረስ ያሉ ንጹሀንን ከየቤታቸው ለቃቅሞ መንግስቴን ሊገለብጡ ነበር ብሎ በግፍ አስሮ ማሰቃየቱ በአብዛኞች ዘንድ የቁጭት ስሜት ቢፈጥርም ውህ የማይቋጥረውን አታካች ፐሮፓጋንዳ ከቁም ነገር የፃፈው እንደሌለ ታውቋል። የኦሮሞ ፌዲራሊስት ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ ሊቀመንበር አቶ ቡልቻ ደመቅሳ ወያኔ መንግስቴን ሊገለብጡ ነበር ብሎ ያሰራቸው ሰዎች ምንም ነገር አድረገዋል ብለው እንደማያምኑ እና ወያኔ ተቋዋሚዎቹን ለማሸማቀቅ ዘወትር የሚሰራው ድራማ ቅጥያ እንደሆነ ለአሜሪካ ድምጽ ገልጸዋል።

በተቃራኒው የመለስን መንግስት ማስወገድ እና ሰው ሀገሩ ላይ በልበሙለነት እና በህግ ጥላ እንዲኖር እንታገላለን ብሎ ዘረኛውና ኋላ ቀሩን አገዛዝ የሚታገሉ የፓለቲካ መሪዎችን ወላጆች፣ ዘመዶች እና ጓደኞችን እንደ አውሬ አድኖ መያዝ ደርግ እንኳን ያልተከተለው ስልት እንደነበር በብዙዎች ተደጋግሞ ሲገለጽ ውሏል። በውጪ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ዘንድ በስፋት የሚነበበው የኢትዮጵያ ሪቭው ድረ ገጽ ላይ እንደተገለጸው፣ ፍጹም አምባገነን ነበር ያልነው ደርግ እንኳ የእነመለስን ቤተሰቦች አላሰረም አላንገላታም። ዛሬ ግን ወያኔ ባለጊዜ ነኝ ብሎ ደርግ በ1970ዎቹ ያልፈጸመውን አረመኔያዊ ተግባር መፈጸሙ የዚህ ጠባብ ቡድን የዘረኝነት ደረጃ ምን ያህል ሥር የሰደደ እንደሆነ ያሳያል ብሎአል።



የፖስታሳጥን ቁጥር :- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

ሃይለ ሀሳብ

## ህገ መንግስታዊ ሥርአታቸው፡ በእረኞች ድንጋይ የሚናድ የሾላ ፍሬ!

ከሙሉነህ ኢዮኤል

### እንደ ሾላ በድንጋይ እንዳይናድ የተፈራለት ‹‹ህገ-መንግሥታዊ ሥርዓት›› የታሪኩ ዳራ

አባቴን የሚያህሉና እንደሱም የማከብራቸው ሰው የአቶ አንዳርጋቸውን አባት የአቶ ጽጌ ሀብተ ማርያምን መታሰር ሰምተው ስልክ ደውለውልኝ ነበር። እኝህ ሰው የአንድ ወቅት የአቶ ጽጌ ተማሪ ነበሩ። አቶ ጽጌ የደብረብርሃን አጼ ዘርአ ያዕቆብ ት/ቤት ዳይሬክተርም መምህርም በነበሩበት ወቀት እሳቸው ተማሪ ነበሩ። ጊዜዉ ከሃምሳ ዓመታት ይበልጣል፡፡

ዛሬ አቶ ጽጌ በሰማንያ አመታቸው ‹‹የግንቦት ሰባት አባል በመሆን መፈንቅለ መንግስት ለማድረግ ሲያቅዱ ከፍተኛ ክትትል ሳደርግ ቆይቼ በቁጥጥር ስር አውያቸዋለሁ›› በማለት መለስ ካሰራቸዉ ሰላሳ አምስት ሰዎች አንዱ መሆናቸው ከንክኗቸው ነበር እኔ ዘንድ ስልክ የደወሉልኝ።

አቶ ጽጌ ሀብተ ማርያም ከዛሬ ሰላሳ አመት በፊት አረመኔው ደርግ በጭካኔ ልጃቸውን አምሃን ገድሎባቸው አስክሬኑን ከብዙ የሬሳ ክምር መሃል እንዲፈልጉ አድርገዋቸው፣ እጆቹ ከትከሻው ተሰባብረው፣ ሮጦ ያልጠገበውን የልጅ ልቡን ያፈነዳውን የጥይት ወጭ 100 ብር አስከፍለው ሬሳውን እንዲወስዱ ፈቅደውላቸው፣ ተመልሰው ደግሞ ከመንግስት እሬሳው እንዳይለቀቅ መመሪያ ደርሶናል ብለው፣ ሳጥን ውስጥ ከገባ በኋላ አስከሬኑን ቀምተው የወሰዱባቸው፣ የልጃቸውን አስክሬን በአግባቡ ለመቅበር እንኳ ያልታደሉ፣ የልጃቸው ሬሳ የወደቀበትን ማወቅ አለመቻላቸው ልባቸውን እንዳስመረረ የኖሩ ልባቸው በሀዘን የተሰበረ የሰማንያ አመት አዛውንት ናቸው፡፡ እኝህ ሰው ብዙ መከራ በህይወታቸው የተፈራረቀባቸው አንዷት ባንዳ ካገባች ልጃቸው በቀር ከሞት የተረፉ ልጆቻቸው በሞላ በስደት በመበታናቸው ወልዶ በልጅ መጦርና መጠየቅ እንዳማራቸው ያን እድል ሳያገኙት የኖሩ፣ ዘመናቸው ሁሉ የሰቆቃ የሆነባቸው፣ በህይወታቸው ከተፈራረቀው መከራ ብዛት ልባቸውን የታመሙ፣ የልብ ህመምተኛ ናቸው።

ብካይ የባንዳ ልጆች ዛሬ አቶ ጽጌን የመንግስት ግልበጣ ተሳታፊ ብለዋቸው ማዕከላዊ ናቸው። እኚህን የቀድሞ ዳይሬክተራቸውና የዛሬዉ የሰማንያ አመት አዛውንት የመንግስት ግልበጣ ዜና ሰምተው ነው እንግዲህ አንድ የማከብራቸው ሰው ስልክ ደውለው ነካክተውኝ ይህን ጽሁፍ እንድጽፍ ምክንያት የሆኑት።

### እንዲህ አይነት ጉድ አዲስ አይደለም ታዲያ ምን ይደንቃል?

ጀርባቸውን ሰርጀሪ ያደረጉ ከሳሎን ወደ መኝታ ቤታቸው ከቤታቸው ወደ መኪናቸው በከዘራ ተደግፈው የሚሄዱ ከእርጅና የተነሳ የአይናቸው ብርሃን እየቀነሰባቸው የመጡ አቶ ነጋ ቦንገርም በስልክ ግንኙነት ሳያደርጉ አይቀሩም በሚል የቁም እስረኛ ሆነዋል። ወ/ሮ አበበች ወልደጊዮርጊስም ለወንድማቸውን አርባ ቤተ ክርስቲያን ሄደው ጸሎተ ፍትሃት ለማድረግ አልታደሉም። ከልጃቸው ጋር ስለ መፈንቅለ መንግስቱ የተነጋገሩት ነገር ቀፎው ውስጥ ይገኝ ይሆናል ተብሎ ተንቀሳቃሽ ስልካቸው ተወስዶባቸዋል። በተለይ የአቶ ነጋም የወ/ሮ አበበችም ስልክ የተቀማው ከልጃቸው ጋር የሶሶስትዮሽ (three way) ስለ መፈንቅለ መንግስቱ ውይይት አድርገው ሊሆን ይችላል ተብሎ ይሆናል። በተለይ አሁን ይህን ሁሉ ሰቆቃ የሚፈጽምባቸው የደርግን ጭቆና ስትቃወም ያ አረመኔው ስርአት ከበላት ከውድ ልጃቸው ከአስካለ ነጋ ጋር በአንድ ክፍል ተማሪ የነበረው መለሰ ዜናዊ መሆኑ እጅግ ሳይቆጫቸው የሚቀር አይመስለኝም። ያች ውድ ልጃቸው የተቃወመችው ስርአት ከደርግ በከፋ ሌላ አፋኝና ዘረኛ አምባገነን መተካቱ፣ የልጃቸው ህይወት ጠፍቶ እርሱን የተካው ከፊተኛው የባሰ አምባገነን ከዚያኛው በተለየ ሁኔታ ደግሞ ዘረኛ መሆኑ እንዴት አያስቆጭ?

### ሌላም አለ፡- ሃጂ መሃመድ ሙሳ፣

ታህሳስ አስር ቀን 1999 ዓ.ም ከአለም በቃኝ ተቀይሬ ወደ ቃሊቲ ዞን ሶስት ከመጣሁ በኋላ የሰማሁት ታሪክ ነው። አቶ መሃመድ ሙሳ ይባላሉ። እድሜያቸው ከሰባ አመት በላይ የሆኑ አዛውንት። ከሀረርጌ ከጭሮ አካባቢ የመጡ አርሶ አደር ናቸው። እኝህ ሰው እዚያው ቃሊቲ ማረሚያ ቤት ህክምና ተከልክለው ከሞቱ ገብዙ እስረኞች አንዱ ናቸው። ሌላ ድርጊት መፈጸም ሳያስፈልጋቸው አሮሞነታቸው ብቻ በቂ ወንጀል ሆኖባቸው በመለስና በበረከት ምክንያት ተፈልጎላቸው ከታሰሩ በሺዎች ከሚቆጠሩ እስረኞች መካከል አንዱ ነበሩ። እኔ እኝህን ሰው ለማየት አልታደልኩም። እኔ እሳቸው ወደነበሩበት ዞን ተቀይሬ ስመጣ ሞተው ነበርና። “ፌዴሬሽንን ለመገንጠል” መሞከር በመባል በሚታወቀው የኦሮሞዎች ክስ የታሰሩ ድንቅ አባት ነበሩ። ከእርሳቸው ጋር በተመሳሳይ ክስ ታስረው የነበሩ ሰዎች ስለ እሳቸው አውርተው አይጠግቡም። ከሜጫና ቱለማ ጋር በተያያዘ ከአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ከታሰሩ ተማሪዎች አንዱ ስለ እሳቸውና ስለ ክሳቸው ብዙ አጫውቶኛል። ከነገረኝ ታሪክ በአጭሩ እዚህ ላይ ላንሳ። ስለሃጂ ማሃመድ የነገረኝ ሰው እሳቸውን እዚያው ቃሊቲ ነው የተዋወቀው።

ሃጂ መሃመድ ህክምና ተከልክለው በክብር የሚገንዝ ወገን በሌለበት እዚያው ቃሊቲ ህየወታቸው እስካለፈበት እለት ድረስ አንገታቸውን እንዳቀኑ፣ ሞራላቸው ሳይሰበር፣ ስለፍትህ ስለእኩልነት፣ ስለሰው ልጅ ክቡርነት እና አብሮ ስለመኖር አስፈላጊነት የሰሟቸውን ሁሉ ታከተኝ ሳይሉ አስተምረዋል። ባይሰማቸውም ለዳኛውም ሳይቀር ነግረውታል። ወንጀላቸው አሮሞነታቸው እንደሆነ ሳይፈሩ ተናግረዋል። ኦሮሞ የሆኑት ደግሞ ፈልገው ሳይሆን ልክ ዳኛውም ሆነ ሌላው ሰው ማንነቱን ሆኖ እንዳገኘው በሚገርም ብስለት አስረድተዋል። በተለይ እኔና በቃሊቲ ማረሚያ ቤት የሰነበትን ስለእሳቸውና እሳቸውን ስለሚመስሉት ሌሎች ብዙ ሺዎች የመዘከር እዳ አለብን።

ስለ ክስሳቸው ጥቂት ልበል። ሃጂ መሃመድ ከአዲስ አበባ ወደ ጅቡቲ በመሄድ ላይ በነበረ ባቡር ላይ ፈንጂ አፈንድታችኋል ተብለው ከታሰሩ 48 ሰዎች መካከል አንዱ ናቸው። አንድ ቦምብ ፈነዳ አሉ። ያፈነዱት ደግሞ አርባ ስምንት ሰዎች ናቸው አሉ። አስቡት አንድ ቦምብ ለአርባ ስምንት ሆነው ሲያፈነዱ። በእድሜ በአስራዎቹ የሚገኙ ልጆችና የሰባ አመት ሃጂ መሃመድ ሙሳ አንድ ላይ ሆነው አንድ ቦንብ አፈነዱ። በተለይ ”ፌዴሬሽንን መገንጠል” በሚባል ክስ የሚወነጀሉ ሰዎች ጨርሶ የማይተዋወቁ፣ አንዱ ከአምቦ ሌው ከሆሮ ሌላው ደግሞ ከሀረርጌ ሌሎቹ ደግሞ ከባሌ ሆነው ነው። ሃጂ መሃመድ በእስር ቤት ውስጥ ታመው የቃሊቲ ማረሚያ ቤት ህክምና እንዳያገኙ ስለከለከላቸው ፍርድ ቤት ውስጥ ለዳኛው እባካችሁ መሞቴ ነው ድረሱልኝ እያሉ ሲለምኑ ልዑል ገ/ማርያም ጥያቄያቸውን ሳይቀበልላቸው ለፍርድ ቤቱ ባመለከቱ በጥቂት ቀናት ህይወታቸው እዚያው ነበር ያለፈው።

እኔ እስከነበርኩበት ቀን ድረስ በእነ ሃጂ መሃመድ ሙሳ መዝገብ ተከሰው ፍርድ ቤት ከሚመላለሱ ሰዎች ውስጥ ሶስቱ እዚያው ቃሊቲ ህይወታቸው ሲያልፍ፣ ሰላሳ ስምንቱ ሰዎች ደግሞ ስምንት አመት ሙሉ በእስር ከማቀቁ በኋላ በነጻ ተሰናብተዋል። የቀሩት ሰባቱ ተከላከሉ ተብለው አንዱ ብቻ እከላከላለሁ ስላለ ፍርድ ቤት ይመላለሳል። ስድስቱ ግን ምን እንከላከላለን የፈለከውን ፍረድብን ስላሉ አንደኛው አስራ ስምንት አመት ሌሎቹ አስራ አምስት አመት ተፈርዶባቸዋል። ዛሬ ቃሊቲ ወይም ዝዋይ ይሆናሉ። አንዳንዶቹ ሞተውም ሊሆኑ ይችላሉ።

### ሌላም አለ እንጂ፡ ጎንደሬው ልጅ ምትኩ

በተለይ ህገ መንግስቱን በሃይል ስለመናድ ሲነሳ አንድ ከግንቦት ምርጫ በኋላ ከጎንደር ተነስቶ አዲስ አበባ ቄራ ካለች እህቱ ዘንድ ሲመጣ ቄራ እንደደረሰ መንገድ ላይ ድንገት አጋዚዎች አግኝተውት የታሰረውን የአስራ አምስት አመት ልጅ የምትኩን ታሪክ ያስታውሰኛል። ምትኩ በዚያች ቀን እርሱ ከመጣበት ጉዳይ ጋር በምንም በማያገናኘው ሁኔታ በማያውቀው ጉዳይ “ህገ መንግስቱንና ህገ መንግስታዊ ስርአቱን በሃይል ለመናድ ሞክረሃል” ተብሎ ልክ እንደ እርሱ ለምን እንደታሰሩ ከማያውቃቸው በእድሜ እርሱን የሚያካክሉ የልጅ ልጆች ካደረሱ ሰዎች ጋር የታሰረ የአስራ አምስት አመት ልጅ ነው።

ምትኩ አመጣጡ ከጎንደር ይሁን እንጂ የገጠር ልጅ ነው። ምትኩ ፊደልም የቆጠረ አልነበረም። ከጎንደር እህቱን ፍለጋ አዲስ አበባ ቢመጣም መድረሻው የእህቱ ቤት አልነበረም። መጀመሪያ አለም በቃኝ፣ በነጋታው ዴዴሳ፣ ከዚያ ዝዋይ፣ ከስምንት ወራት በኋላ ደግሞ ተመልሶ አለም በቃኝ ከዚያም አለም በቃኝ ሲፈርስ ቃሊቲ ቤቱ ሆነ። ምትኩ ከአለም በቃኝ እስር ቤት ወደ ፍርድ ቤት ህገ መንግስቱን በሃይል ለመናድ ሞክረሃል ተብሎ ይመላለሳል። ወንጀሉ ሲዘረዘር ደግሞ ድንጋይ በመወርወር፣ አውቶብስ በማቃጠል...ወዘተ ይላል። ከየትኛውም ስለሌለበት የሚሉት ገብቶት አያውቅም። ሁል ጊዜ እስረኞች ፍርድ ቤት ሲቀርቡ ችሎቱ ከተሰየመ በኋላ ክሳቸው ተነቦ ተከሳሾች የእያንዳንዳቸው ስም እየተጠራ በእለቱ መገኘታቸው ስለሚጣራ ፍርድ ቤት በቀረበ ቁጥር ህገ መንግስቱን ለመናድ፣ ድንጋይ በመወርወር አውቶብስ በማቃጠል...ወዘተ መባሉ ይከነክነዋል።

አንድ ቀን አላስችል ብሎት ተከሳሾች መልስ እንዲሰጡ ሲጠየቁ እሱም እጅ አወጣ። እጅ ያወጣው የቀረበበትን ክስ ለመከላከል ሳይሆን በውስጡ የሚከነክነውን ጥያቄ ለመጠየቅ ነው። ክሳቸውን የሚያየው ችሎት መሃል ዳኛ አሰፋ አብርሃ ይባላል። እንዲናገር እድል ሲሰጠው ቆመ። ሰው ሁሉ ከመናገሩ በፊት ክቡር ፍርድ ቤት እያለ እንደሚጀምር በእነዚህ ፍርድ ቤት በተመላለሰባቸው ጊዜያት ተምሯል። እርሱም እድሉ ሲሰጠው እንደሌሎቹ ክቡር ፍርድ ቤት ለማለት ፈልጎ ክቡር ፍርድ ቤት የምትለዋ ሀረግ ጠፋችበት። ፍርድ ቤቱን ለማክበር አንድ ነገር እንደሚባል ስለገባው ብቻ “ጋሼ ፍርድ” ቤት ብሎ ጀመረ። “ጋሼ ፍርድ ቤት ህገ መንግስቱ የሾላ ፍሬ ነው እንዴ በድንጋይ የሚናደው ሲል” ይጠይቃል። የልጁን ጥያቄ የሰማ ሁሉ በሳቅ ነበር የፈነዳው - ከመሃል ዳኛው አሰፋ አብረሃ በቀር። ‹‹ህገ መንግስት›› የሚባል መንግስት ከሚህል አስፈሪ ነገር ጋር የተቆራኘ ነገር የሾላ ፍሬ ይመስል በድንጋይ (ያውም እንኳን እርሱ ሊወረውር ቀርቶ ሲወረወር ያላየው ድንጋይ) ናድከዉ ተብሎ ሲከሰስ ታድያ ምን ይበል? ያ ልጅ ዛሬ ይፈታ እዚያው ቃሊቲ ይሁን አላውቅም።

## ምን ይደንቃል? ምንስ ቢሉ ምን ይገርማል?

ታዲያ ዛሬ አቶ ጽጌ በመንግስት ግልበጣ ተጠርጥረው ታሰሩ ቢባል ምን ይደንቃል? አቶ ነጋም ሆኑ ወ/ሮ አበበች የቁም እስረኛ ቢሆኑ ማን ነው የሚገርመው? ጀኔራል ተፈራ ማሞ፣ አቶ መላኩ ተፈራ፣ ሃጂ መሃመድ ሙሳም፣ ጎንደሬው ልጅ ምትኩ፣ በቃሊቲ ሲኦል በዴዴሳ ጫካዎች፣ በደንቆሮ ዋሻ፣ በብር ሸለቆ ሀሩር የሚነዱ ሌሎች ለአገርና ለወገን የሚፈይድ አንዳች ነገር ለመፍጠር የሚሆን አእምሮ በሌላቸው መለስና በረከት በሚባሉ ብካዮች ወንጀል እየተፈረከባቸው ዘብ ጥያ የወረዱ ሺዎች ጥፋታቸው ምንድነው? ከተባለ የሚከተሉት ነገሮች ብቻ ናቸው ሊሆኑ የሚችሉት።

1. ጀኔራል ተፈራ፣ ሃጂ መሃመድ፣አቶ ጽጌ፣ አቶ ነጋ፣ አቶ መላኩ እና ሌሎችም አማራ፣ኦሮሞ፣ጉራጌ ወይም ሌላ መሆናቸው፣
2. ባርነትን በጸጋ ተቀብሎ ለመኖር የማይፈቅዱ፣ አልያም
3. ባርነትን ተቀብሎ ለመኖር ፈጽሞ አይቻለንም የሚሉ ልጆች የወለዱ መሆናቸው ነው።

(ወደ ገፅ 4 ዞሯል)

***ህገ መንግስታዊ ሥርአታቸው፡ በእረኞች ድንጋይ የሚናድ !.........(ከገፅ 3 የዞረ)***

እርግጥ አቶ ጽጌ ደግሞ ሌላም ጥፋት አለባቸው። ፋሽስት ጣልያንን ሲዋጉ የተሰው የአርበኛው ሀብተ ማርያም ተሰማ ልጅ ማን ሁኑ አላቸዉ? እነ መለሰ ደግሞ ለፋሽስት ጣልያን ወዶ ገብ፣ የባንዳ ልጆች ናቸው። የባንዳ ልጆች ደግሞ የበታችነት መንፈስ ሁል ጊዜም ይከሳቸዋል። የአርበኛ ልጅ ምንም ባያደርጋቸው እንኳ በህይወት መኖሩ ብቻ ህሊናቸውን ሲጠቀጥቃቸው፣ የባንዳ ልጆች መሆናቸውን ሲያስታውሳቸው ይኖራል። እነርሱ ደግሞ ከህሊናቸው ጦርነት "ናጽነት" የሚወጡ የሚመስላቸው አርበኛን ከነልጆቹና ከነህገሩ ሲያጠፉት እንደሆነ ይሰማቸዋል። ታማኝነት በዘር ነው ብለው ስለሚያምኑ ደግሞ ከእነርሱ ውጭ ያለውን ሰው ሁሉ ይጠረጥሩታል። ባለፈ ባገደመ ቁጥር መንግስታቸውን የገለበጠ ይመስላቸዋል። ህገ መንግስታቸው ደግሞ በዘር ታማኝነት ላይ የተገነባ ስለሆነ ሁል ጊዜም እንዳይናድባቸው ይፈራሉ። አብረው በጋራ ያልሰሩት ቤት ሁሌም እንደሚፈራርሰው እንዲሁ ዘረኞች እንገነባለን የሚሉት ህገ መንግስትና ህገ መንግስታዊ ስርአት እረኞቹ እነ ልጅ ምትኩ እህታቸውን ለመጎብኘት ከጎንደር አዲሳባ በመጡ ቁጥር፣ የአማራ አልያም የኦሮሞ ጄኔራሎች መንገድ ላይ ሲሄዱ የሚያሰሙት ኮሽታ፣ ባርነትን አንቀበልም የሚሉት የአርበኛ የልጅ ልጆች ካሉበት ሆነው ከሚያሰሙት ጩሀት ጋር ተዳምሮ መንግስታቸው የተገለበጠባቸው እየመሰላቸው በድንጋጤ ሚይዙትን ሚጨብጡትን አሳጥቷቸዋል። ትናንት በሁለት ሺ ብር አብዮት ሊያካሄድ ነው ብለው ያላጋጡበትን ድርጅት "መንግስት ሊገለብጥ ሲል ደርሼ አከሸፍኩበት" ሲሉ አለም በአግራሞት ሰምቷቸዋል። አሁን አሁንማ መለስ አይደለም ሌላን ሰው የገዛ ራሱን ጥላ ማመን እየከበደው መጥቷል። በጋምቤላ ከአኙዋክ መወለድ ወንጀል ሆኖባቸው በደማቸው በጸሃይ ሀሩር የነደዱ የጋንቤላን በረሃዎች ያረጠቡት የአኙዋክ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ለአምላካቸው የሚያሰሙት የተበቀልልን ጩሀት ከጋምቤላ እስከ ዲሲ ዘልቆ እነ ጄኖሳይድ ዎችን የተኛ ፋይል ቀስቅሰው የእስር ማዘዣ በመለስ ላይ ይውጣበት የሚል ተማጽኖ እንዲያሰሙ አድርጓቸዋል። እነ መለስ በዚህ ሁሉ ጩሀት እየባነኑ እንቅልፍ እያጡ ማደር ጀምረዋል። ለዚህም ይመስላል ከመለስ ቢሮ አከባቢ ከወትሮው ለየት ባለ መልኩ ከቆሻሻ መጣያዎች ውስጥ የሚገኙት "ወይኔ ጉዴ" የሚሉ በመለስ የእጅ ጽሁፍ የተጻፉ መሆናቸው በደህንነት ሰዎቻችን የተረጋገጡ ብጫቂ ወረቀቶች እየተገኙ ያሉት። በተለይ "ማን ተይዞ ማን ሊቀር" በሚል ከትናንት ጀምሮ ማንም የወያኔ ባለስልጣን ወደ ውጭ ሀገሮች ለመሄድ ሲዘጋጅ ከመውጣቱ በፊት አስቀድሞ እንዲያሳውቀው የደህንነት ሹሙ ጌታቸው አሰፋው በመለስ እንደተነገረው እየሰማን ነው። እነ መለስ የቱንም ያህል ስሙን አንቆለጳጵሰው ቢጠሩት፣ "ህገ መንግሥታዊ ሥርዓታቸው" እንደ ጎንደር እረኞች የሾላ ፍሬ ክምር ከመናድ በቀር ሌላ ምን ምርጫ አለው? የመለስ እጣው በደንብ ወለል ብሎ እየታየ ነው። ቀኑን በውል ባያውቁትም የጄኖሳይድ ዎቹ ግሬጎሪ ስለነ መለስ መጨረሻ እንዲህ ሲሉ ተንብየዋል፦

*ያውና ኢያለሁ መለስን ሲሄድ በዴንሃግ ጎዳና፣*
*ቀኙ ከበረከት ግራው ከስብሃት ተጣብቆ በካቴና፣*

ያሰንብተን! ሙሉነህ ኢዮኤል ከዋሽንግተን ዲሲ

**ለወያኔ በጀት ምደባ አድሎአዊነት እንዲመችና ቀጣዩን ምርጫ ተብዬ ወያኔ አንደማያሸንፍባቸው የገመታቸውን ክልሎች..................... (ከገጽ 1 የዞረ)**

<<የጉራጌ ህዝብ ቁጥር መቀነስ በጣም አጠያያቂ ነው። እንዴት ነው፤ የጉራጌ ህዝብ አይወልድም፤ አይጋባም፤ አይባዛም?>> የሚል ጥያቄ በማቅረብ ላይ እንዳሉ በወያኔው አሽከር ተሾመ ቶጋ <<ጥያቄዎ የፓርላማውን ክብር የሚነካ ነው እና ያቁሙ>> ተብለው ለማቆም ተገደው እንደነበር በመግለጽ፣ የውስጥ አዋቂ ምንጮች ከተዛባው ቆጠራ በስተጀርባ የወያኔ የበቀል አሰራር ሳይኖር እንዳልቀረ አስታውቀዋል።

የኢትዮድያ ህዝብ ከዳር እስከ እስከ ዳር ወጥቶ ህዝበ ውሳኔውን በኋላ ቀሩ እና በዘረኛው አምባገነን መለስ ዜናዊ አገዛዝ ላይ ባስተላለፈበት በምርጫ 97፤ የጉራጌ፣ የአማራ እና የአዲስ አበባ ህዝብ ከሌሎች ክልሎች በተለየ ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ቅንጅትን መምረጡ ይታወቃል። ከምርጫው በኋላ ባሉት ወራትም ወያኔ በአማራውና በጉራጌው ህዝብ ላይ የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ ዘመቻ መክፈቱ ይታወሳል። የወያኔ ዘረኛ ፖሊሲ ዋና አስፈፃሚ ከሆኑት ውስጥ አንዱ ተፈራ ዋልዋም፣ ወደ ሃዋሳ ከተማ ሄዶ ለክልሉ ነዋሪዎች ባደረገው ንግግር፣ አማራዎች እና ጉራጌዎች ትምክህተኞች እንደሆኑ መናገሩ ይታወቃል።

ለይስሙላ በቆመው የወያኔ የፌዴራል አገዛዝ መሰረት አንድ አካባቢ ባለው ነዋሪ መሰረት በጀት እንደሚመደብለት እና የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተብዬው ውስጥ የሚያገኘው መቀመጫ ቁጥርም እንደሚወሰን ይታወቃል። ወያኔ የነዚህን ህዝቦች ቁጥር የማሳነስ ስራ የሰራውም የነዚህን አካባባቢዎች ህዝቦች ስነልቦና ለመጉዳት እና በጀታቸውን ለመቀነስ፤ እንዲሁም የውክልና መብታቸውን ለመንፈግ እንደሆነ በብዙዎች ተገልጿል።

የአዲስ አበባ ህዝብ እንዴት በ2.5 ሚሊዮን ህዝብ ሊቀንስ ቻለ ተብሎ መለስ ዜናዊ ሲጠየቅ <<አብዛው ቀን ቀን አዲስ አበባ የሚታየው ህዝብ ሲመሽ ለስራ ከመጣበት የአዲስ አበባ ጎረቤት አካባቢዎች ይሄዳል። እንደዚህ ያሉ አጋጣሚዎች በሌሎች ትልልቅ ከተሞችም ይከሰታል። ለምሳሌ ቶኪዮን ብንወስድ ከአዲስ አበባ ጋር ተመሳሳይ ነው። ቀን ላይ በርካታ ህዝብ ቢታይም ከ2 ሚሊዮን በላይ ሲመሽ ቶኪዮን ለቆ ይወጣል፤>> ብሎ እንደነበር ያስታወሱት ታዛቢዎች እንደቶኪቶ ያለ እጅግ ዘመናዊ እና ፈጣን ባቡር ባለበት ከተማ ሁለት ሚሊዮን ህዝብ ከከተማዋ ወጥቶ በበነጋታው ቢመለስ አይገርምም።በአዲስ አበባ ለምሳሌ ከደብረዘይት እና ዱከም ህዝብ የሚያመላልሱ አውቶቢሶች ሁለት ናቸው። እነሱም 68 እና 25 ቁጥር የተባሉ የአንበሳ አውቶቢሶች ናቸው። ሁለት አውቶቢሶች ደግሞ ከ400 ሰው በላይ መውሰድ አይችሉም ሲሉ የተለመደውን የመለስን ጥራዝ ነጠቅ መልስ አጣጥለዋል።

***ወያኔ በመፈንቅለ መንግሥት ሴራ ከተከሰሱት ብርጋዴር ጀነራል ተፈራ ማሞ ጋር ንኪኪ ይኖራቸዋል በሚል ጥርጣሬ በአገር መከላከያ ሠራዊት ውስጥ ከከፍተኛ እስከ ዝቅተኛ ማዕረግ ያላቸውን የመመንጠር ዘመቻ ተያይዞአል ። በጥቃቱ አማርኛ ተናጋሪው ዋና ስለባ እንደሆነ ........... (ከገፅ 1 የዞረ)***

የግንቦት 7 ንቅናቄ መላው የሰራዊቱ አባላት በተባበረ ክንድ ይህን የወያኔ መሰሪ ዓላማ ለማክሸፍ ካልተረባረበ እነ መለስ ዜናዊን በመሳሰሉ ዘረኞች እና ለአገርና ለወገን ፍቅር በሌላቸው ምንደኞች አንድ በአንድ እየተመታ ወደ ልመና ተግባር እንዲሰማራ እንደሚደረግ ከወያኔ የደህንነት ምንጮች የተገኘውን ይህን መርጃ ይፋ ማድረግ መርጦአል ።

ይህ በ እንዲህ እንዳለ በመከላከያ ሰራዊቱ ውስጥ ከዘጠኝ አመት በላይ አገልግለው በግዳጅ ላይ እና በጦር ሰፈር ባጋጠማቸው መረን የለቀቀ ዘረኝነት የተነሳ ባለፈው አመት ከወያኔ ሰራዊት ስንበት ጠይቀው እንደወጡ ለአዲስ አበባ ዘጋቢያችን የገለጹት አንድ የመቶ አለቃ ወያኔ ትንሽ ችግር በገጠመው ቁጥር ዘርን መሰረት ያደረገ እርምጃ እንደሚወስድ የታወቀ ነው ብለዋል።በ1990 አመተ ምህርት የካቲት ወር ሰራዊቱን ለመቀላቀል የሚያስችላቸውን ስልጠና በሁርሶ የመኮንኖች የማሰልጠኛ ጣቢያ እንደተከታተሉ የተናገሩት የመቶ አለቃ ዘረኝነቱ ከማሰልጠኛ ጣቢያ እንደሚጀመር ይገልጻሉ።በማሰልጠኛው ጣቢያ ወታደራዊ የቴክኒክ ስልጠና በቀድሞ ወታደሮች ሲሰጥ የፓለቲካ ስልጠና ግን ሙሉ በሙሉ በወያኔ ሀላፊዎች ይሰጣል ።ወታደራዊ ስልጠናውን በሙያቸው ብቃት ብቻ ተመርጠው የሚያሰለጥኑት በፊትም እዛው ትምህርት ቤት ይሰሩ የነበሩ ብቁ መኮንኖች እና ከተለያዩ ብሄረሰቦች የመጡ ነበሩ።የፓለቲካ ትምህርቱን የሚሰጡት ግን ሙሉ በሙሉ ለማለት በሚያስደፍር ሁኔታ ከአንድ ብሄረሰብ የመጡ ነበሩ ።በአዋሽ አርባ የከባድ መሳሪያ ማሰልጠኛም ተመሳሳይ አሰራር እንዳለ ገልጸዋል።በጣም የሚገርመው አሉ መቶ አለቃው በጣም የሚገርመው ለግድጃ ለረጅም አመት በቆየሁበትም የዛላአንበሳ ግንባር ከፍተኛ ፤መካከላኛ እና እስከ 50 አለቃ ያለው ማእረግ በጠቅላላ በአንድ ብሄር ሰዎች መያዙ ነው ይላሉ።

ለዘጋቢያችን ምሬታቸውን የገለጹት እኚሁ የመቶ አለቃ ከሰሞኑ ወያኔ መፈንቅለ መንግስት አድርጋቻሁ ከስልጣኔ ልታባርሩኝ ነበር ብሎ በተለይ አማራ የመከላከያ ሰራዊት መኮንኖችን እና ወታደሮችን ማሰሩ በተመለከተ ያላቸውን አስተያየት ተጠይቀው<<በተለይ ከሌላ ብሄረሰብ በመጣው የመከላከያ ሰራዊት አባል አካባቢ ከፍተኛ ቁጭት እንዳለ አያጠያይቅም።ባለፈው ብርጋድየር ከማል ገልቹ ከዳ ተብሎ የኦሮሞ መኮንን እንዳለ በአይነ ቁርኛ ይጠበቅ ነበር እንደ ጄኔራል አለም እሸት ደግፌ ያሉ ደግሞ ተለቃቅመው ታሰረው ነበር።አሁን ደግሞ ተራው የአማራው ይመስላል።የተባለው መፈንቅለ መንግስት መደረገ አለመደረጉን አላውቅም።አሁን ካልተደረገ ግን ያለውን ብሶት እና ቁጭት ለተመለከተ አንድ ቀን ወያኔን መንግሎ የሚጥል ትልቅ አመጽ ከመከላከያ ሰራዊት መነሳቱ የጊዜ ጉዳይ ብቻ ይመስለኛል>>ብለው አስተያየታቸውን አጠቃለዋል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

በ17870 KHZ በ 16 ሜትር ባንድ እና በ18350 KHZ በ19 ሜትር ባንድ ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

**ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን።**

g7radio@ginbot7.org